# ኢየሱስ ማነው?

በዚህ ባለንበት ወቅት ይሕ ጥያቄ የሁሉ ጥያቄ ነው። ሁሉም በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት እንዲያስችለው እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምን እንደሆነ በአግባቡ መረዳት አለበት። ይህ ጥያቄ የእኛ እያንዳንዳችን አለም እንደሚጠይቀው ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ስለእርሱ ማንነት ሰዎች ምን እንደሚሉ ጠይቋቸዋል። ለሐዋርያትም የቀረበው ይህ ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር።

"ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል?" እነርሱም" "አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎችም ኤልያስ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" አሉት። ማቴ 16፥14-15 ይህ ሰዎች የሚሉት ትክክለኛ ማንነቱን ያልተረዱት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን "እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ?" አላቸው። ይህ ጥያቄ እጅግ በጣም ወሳኝ ጥያቄ ነበር። የእርሱን ማንነት እንዴት እንደሆነ የሚናገሩበት ጥያቄ ነበርና ሲመልሱም "አንተ በእውነት የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት ነበር። ማቴ 16፥16-18 ጌታም መልሶ "ይህን ሥጋና ደም አልገለጠልህም የሰማዩ አባቴ እንጂ" ሲል ለጴጥሮስ ተናግሮታል። እዚህ ጋር አንድ ነገር በጣም እናስተውላለን፡-

አንደኛ - ሰዎች እነርሱ እንደመሰላቸው ብዙ ዓይነት መግለጫ ለርሱ እንዳቀረቡ

ሁለተኛ - ትክክለኛውን መልስ ላገኙት ለሐዋርያት ለተሰጣቸው ምላሽ ሥጋና ደም መግለጥ የሚችለውን ሳይሆን ከሰማዩ አባት የተሰጠ መልስ መሆኑን እንረዳለን።

አሁንም በዚህ ጥያቄ ላይ ሥጋና ደም የሚገልጠውን፣ እውቀት የሚያመነጨውን ሳይሆን ከሰማይ አባታችን የተሰጠውን እውነተኛ መልስ

በዲያቆን አሐዱ አስረስ፡-

www.ethiopianorthodox.org

የመዳን ምሥጢር ላይ እንደገለጽነው በሕይወታችን ዘመን ስንኖር የምንሰራው ኃጢአት ሲሆን ይህም በንስሀ የሚወገድ ነው። ጥንተ አብሶ ኃጢአት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ቁስልና ሞት በትንሣኤውም የተወገደ ነው። ይህ ኃጢአት የዘላለም ሞት አሳውጆብን የነበረ ኃጢአት ነውና ስለዚህ ሁለቱን አጥርተው ቢለዩአቸው ክርስቶስንም በትክክል ለይተው ይረዱት ነበር።

- ዕብ 5፥7 "እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ። እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ ተሰማለት ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ። ከተፈፀመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው" እነዚህ ሁሉ በሥጋው ወራት በምድር ሲመላለስ የፈፀማቸው መሆኑን በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው። እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ ተሰማለት ማለቱ አዳም እግዚአብሔርን ባለመፍራቱ ደፍሮ በልቶ ነበርና እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ጉልበት አቅም ኃይል እያለው እንደሌላው በመሆን ራሱን ዝቅ አድርጎ መታዘዝን አሳይቶአልና። መጽሐፍም እንዲህ ይለናል። "በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።" ሮሜ 5፥19 አንዱ ያልታዘዘው አዳም ነው አትብላ የተባለውን በልቶአልና አንዱ የታዘዘው ክርስቶስ ነው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ራሱን ባዶ አድርጎ ስለእኛ ሞቶአልና። ሞት የመጣው ባለመታዘዝ ምክንያት ነበርና ለሚታዘዙ ሁሉ ይድኑ ዘንድ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው ያለው ለዚህ ነው። አባቶቻችንም ሲናገሩ "ከመሥዋዕት መታዘዝ ይበልጣል" ይሉናል። ክርስቶስ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያና መጨረሻው እርሱ ስለሆነ ከእርሱ ውጪ ከእርሱ በላይ ማንም የለም። ፈራጅ እንደ ሥራው ለሁሉ የሚከፍል እንጂ ስለኛ



ኃጢአት የሚለምን አይደለም። "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" ከዚህ በላይ ምን ያስፈልግ ይሆን? አማላጅ ብለው የሚያምኑ ራሳቸውንና እምነታቸውን እንዲመረምሩ እንጠይቃቸዋለን። የሚያምኑት እምነት ራሱ እርስ በርሱ ይጋጫልና። ክርስቶስ ኢየሱስ ወልድ ከሶስት አካል አንዱ አካል መሆኑን አምላክ ፈጣሪ ከአብ ጋር በእሪና እኩል መሆኑንና ራሱ እግዚአብሔር መሆኑ እያመኑ ፍጹም በተቃረነው ደግሞ አማላጅ ነው ብሎ ማመን ሁለቱ ፍጹም ይቃረናል። ስለዚህም ነው እምነታቸውንና ራሳቸውን እንዲመረምሩ የጠየቅናቸው። አማላጅ ከሚለው ቃል ጋር መምጣት አንስቶ እምነቱ አብሮ ተመሥርቶአለና የቀደመውን ግን ባለመመርመር ብዙዎች እየጠፉ ነውና። ለዚህም ይመስለናል ከሙሉ ወንጌል አማኞችና ከሌላው የጴንጤ ቡድን ውስጥ የእምነት ሠራዊት (Faith Armay )የአሸናፊዎች መቅደስ(Winner Chaple) አሴምብል ቸርች የመሳሰሉት ተገንጥለው የወጡት። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሷም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ ብዙዎች ግን አንሔድባትም አሉ።" ኤር 6፥16 መንገድ ያለው ሃይማኖትን ነው የቀደመውን እምነት በመጠየቅ ትክክሉን መረዳት ይቻላል። ልብን እልከኛ ማድረግ ግን ጥፋት ነው "መንፈስን አታጥፉ ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ ከማናቸውም አይነት ክፉ ነገር ራቁ።" 1ተሰ 5፥19 ይህ ምክር ታላቅ ነውና የእግዚአብሔርን እውነት ማጥፋቱ የተገባ አይሆንምና ሁሉን ፈትኖ መልካሙን ሃይማኖት መያዝ ይበጃል፣ያድናል።



www.ethiopianorthodox.org

ይለናል። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ዮሐ 1፥1 ይህ ቃል ክርስቶስ ኢየሱስ ነው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ፈጣሪ መሆኑን ሲናገር አብ ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ይለናል። "ጌታ ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮችንም የእጅህ ሥራ ናቸው እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጎናፀፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጣማል አንተ ግን አንተ ነህ አመቶችህ ከቶ አያልቁም" ዕብ 1፥10-12 ይህ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር የሰማይ ፈጣሪና ገዥ የእነርሱም አሳላፊ መሆኑን ያስረዳናል። ታዲያ እንደ ይሆዋ ምስክሮች አገላለጽ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የእነዚህ ሁሉ ፈጣሪ አይለደለም ባለቤትም አይደለም ማለት ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ይላል ዘፍ 1፥1 ስለዚህ የምድርና የሰማይ ፈጣሪ አንድ እግዚአብሔር ከሆነ ክርስቶስ ከሶስቱ አካል አንዱ አካል ሰው ሆኖ በመገለጡ ፈጣሪ አይደለም ሊባል አይችልም። ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው በመሆን ታየ እንጂ።

የሰው ፈጣሪ ነው። "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" ኤፌ 2፥10 ይህ የኛ ፈጣሪ ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን ያመለክተናል። ይህም ክርስቶስን በፈጣሪነቱ እንድንረዳው ሁላችንን ለማሳወቅ ነው።

1.3.2 <u>ክርስቶስ አምላክ ነው። ሱታፌ አምላክ ሳይሆን ፈጥሮ የሚገዛ አምላክ ነው ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል።</u>

"አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን" ሮሜ 9፥5 ከእነርሱ



በሥጋ መጣ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳም መልካምና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ዘፍ 3፥22 ባለው ቃል መሠረት ከሶስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ በተለየ አካሉ የሰውን ሥጋ መልበሱን ለማመልከት ሲሆን ይህም ትውልድ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅ፣ ከያዕቆብ ከተቀደሱ ሰዎች ወገን መሆኑን ለማመልከት ነው። ከሁሉ ከላይ ሆኖ ብሉአልና ከእርሱ በላይ ማንም የለም። "ለዘላለም የተባረከ አመላክ" እንዳለው አምላክነቱን ጊዜ ሰጥቶት ጊዜ የሚወስድበት አይደለም። ለምሳሌ ሙሴን በፈርኦን ላይ አምላክ እንደሚያደርገው በዘፀ 7 ላይ እግዚአብሔር ተናገሮታል። ይህ አምላክነት ግን የጸጋ አምላክነት እንጂ ፈርኦንን ሙሴ ስለፈጠረው የተነገረ አይደለም። አንዳንዶ የክርስቶስን አምላክነት ከሙሴ አምላክ አደርግሃለሁ ካለው ጋር ያገናኙታል። ነገር ግን ፍጹም የማይገናኝና ልዩነት ያለው ነው። ሙሴ እግዚአብሔር በሰጠው ተአምራት በፈርኦን ላይ የበላይ ሆኖ እንደሚያሸንፈው ለመግለጽ የተነገረ ነው። ክርስቶስ ግን ፈጣሪ እንጂ ፍጡር ያልሆነ ዘላለማዊ አምላክ ነው።

"የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁን ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።" ቲቶ 2፥1-13 ይኸም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና መድኃኒት መሆኑን ይህም የተባረከው ተስፋችን እንደሆነ ያስተምረናል።

በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ 2ጴጥ 1፥1 ግልጽ በሆነ መልኩ ክርስቶስ ማነው? ብንል አምላክና መድኃኒት መሆኑን ያሳየናል።

"እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።" 1ዮሐ 5፥20 አስተውል እውነተኛውና ብቸኛው አምላክና የዘላለም ሕይወት እርሱ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ሁሉ ተገዝቶአል ሲል ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጽ ነው። ሁሉም ምንም እንኳ ለሞት ቢገዛ ሁሉን ያስገዛለትን ግን አምሮ በመቃበር ሊያስቀረው አልቻለም። በሶስተኛው ቀን ተነሥቶአልና ሞትና መቃብርን ፈንቅሎ በሥልጣን ወጥቶአልና። ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሶስት ቀን አስነሣዋለሁ እንዳለ።

መ. ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን ለሞት ሁሉ ስለተገዛ

ሠ. ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ እያንዳንዱ ነገር ይፈፅም ዘንድ ሞትም ድል ይነሳ ዘንድ

ረ. ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል በበላህ ጊዜ ትሞታለህ ዘፍ2፡17 እንዳለው በመብላቱ ሞተ። ለሞት ሁሉን አስገዛለት ስለዚህም ክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉ እንዲገዛለት ላደረገው ሞት ተገዝቶ ሞቱ በመቃብርም ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት አድሮ በሶስተኛው ቀን ተነሣ ይህ ጥቅስ ስለ ሞት የተነገረ እንጂ አብ ወልድን ይገዛዋል ማለት አይደለም። መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። ማቴ 22፡29 እንዲህ ካለ ስህተት ያድነን።

ራዕ 3፡14 በእግዚአብሔር ፍጥረት የነበረው እንዲህ ይላል። አሁንም ይህን ጥቅስ የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ፍጡር ነው ለማለት የሚጠቀሙበት ጥቅስ ነው። በእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው ማለት መኖሩን በፊትም ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንጂ ፍጡር ነው ሊያሰኝ የሚችል አንዳችም መልዕክት የለውም። ለራሳቸው ጥፋት ወንጌሉን ያጣምማሉ እንደተባለ አንዱም ቃሉን ያጣምሙታል እንጂ ቃሉ የሚገልጸው በፍጥረቱ መጀመሪያ የነበረ መሆኑን ነው። እንዲሁ ራዕ22፡12 "መጀመሪያውና መጨረሻው አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ" ይላል እንጂ ፍጡር ነው ለማለት የሚያስችል አንዳችም ሃሳብ የለም ፈጣሪ ጌታ እግዚአብር ምርስ ብቻ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ይሁ 1፡26



www.ethiopianorthodox.org